# ሙሽር ለመድሽ አሉ



እንደ ሞተ አሳማ- የከረፋው ጸጉሩ
አረንጓዴ ማሳ- የመሰለው ሽግኑ
ዝናብ ያጣ ደባይ- ንቃቃታም እግሩ
እድል ቀን ጥሎለት- ባለመትረይሱ
ዘራፍ ባዩ “ጀግና”
በዘረፈው ቅቤ-የራሰው ራሱ
እኔን ቀን ሲጥለኝ እርሱ ቀና አለና
ጠልፎ ወስዶሽ ቆንጆን -ሚስቱ ካደረገሽ
አዱኛሽ ሳትባይ- ከቤቱ አስገብቶሽ
አስርተ- ዘመናት- አሃዱ ክሌቱ
ዘመን ተቆጠረ- ሆነሽ እንግልቱ
ልብሽ ተስፋ ቆርጦ- ጀግና ባያይ አይንሽ
ሰው ሁሉ መስሎታል- በትዳር የለመድሽ

እና ሰማሁ ወሬ- ወሬ አይደበቅም- ወሬ ተሰማ አሉ
ሙሽር ለመድሽ አሉ
ሚስት ሆነሻል አሉ።

እንደ ወንድ ባልፎክር- መውዜር ባላነሳ
ደሜም ቱግ ባይል-ለጠብ ባልነሳ
ይድረስሽ ሃዘኔ- እሮሮየን ስሚው
ጠላፊው ቤት ገብተሽ- ሙሽር "ለለመድሽው!"


ዳግማዊ ዳዊት
መጋቢት 2005 ዓ.ም.
Ethio_dagmawi@yahoo.com